የፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

# የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
# የ2011 በጀት ዓመት ሂሣብ
# ኦዲት ሪፖርት

ሚያዚያ/2012 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

## የ2011 በጀት ዓመት የኦዲት ሪፖርት

### መግቢያ

የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የተመደበለት በጀት በፋይናንስ አዋጅ፤ ደንብ እና በተከታታይ በወጡ መመሪያዎች መሠረት ለታቀደለት ዓላማ መዋሉን እንዲሁም ሂሳቡ በመንግስት የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት መያዙንና የመንግስት ሀብትና ንብረት በሚገባ መጠበቁን ለማረጋገጥ ከዚህ ሪፖርት ጋር የተያያዙትን የ2011 በጀት ዓመት የሂሳብ ሪፖርቶች እና የሂሳብ ማስታወሻዎችን ኦዲት አድርገናል፡፡

የሂሳብ ሪፖርቶቹን የማዘጋጀት ኃላፊነት የፍ/ቤቱ ሥራ አመራር ሲሆን፤ የሂሳብ ሪፖርቶቹን ኦዲት በማድረግ የኦዲት አስተያየት መስጠት ደግሞ የዋና ኦዲተር ኃላፊነት ነው፡፡

ኦዲቱ የተከናወነው የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ስልጣንና ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን መሠረት በማድረግና የዋና ኦዲተርን የኦዲት ስልት በመከተል ነው፡፡

እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ላይ አጥጋቢ የሆነ ማረጋገጫ (የኦዲት አስተያየት ) ለመስጠት ያስችለናል፡፡

ለኦዲቱ ሥራ መሠረት የሆኑት ኮሚሽኑ ያቀረባቸው የሂሳብ ሪፖርቶች፤ መዛግብት እና ደጋፊ ማስረጃዎች እንዲሁም በኮሚሽኑ ሥራ አመራር የተሰጡ ማብራሪያ ናቸው ፡፡

ኦዲቱ የተከናወነው የዓመቱን የሂሳብ እንቅስቃሴ ሊወክሉ የሚችሉ ናሙናዎችን በመውሰድ በጥልቀትና በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው፡፡

የሚከተሉት የፍ/ቤቱ የሂሳብ ሪፖርቶች ከዚህ የኦዲት ሪፖርት ጋር ተያይዘው ቀርበዋል፡፡

- የገቢ ሂሳብ ሪፖርት፤
- የወጪ ሂሳብ ሪፖርት፤
- የተሰብሳቢ ሂሳብ ሪፖርት
- የተከፋይ ሂሳብ ሪፖርት፤
- የሂሳብ ሚዛን ሪፖርት፤
- የዝውውር ሂሳብ ሪፖርት

የፌዴራል ዋና ኦዲተር
የፋይናንስ ኦዲት
መ/ቤት

**ለኦዲት አስተያየቱ መሠረት የሆኑት ጉዳዮች፣**

የፍ/ቤቱ የሂሳብ ሪፖርቶች ጉልህ የሆነ ግድፈት የሌለባቸው፣ በአዋጅ በተፈቀደው በጀት እና በመንግሥት ሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት የተዘጋጁ እና የተሰበሰበው ገቢ፣ የተከፈለው ወጪና የበጀት አጠቃቀሙ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅን፣ ደንብና መመሪያን የጠበቁ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

**ገቢ፤**

1. **ገቢ ያልተደረገ የጉዳት ካሣ ብር 5,279,007.38**

   **በከፍተኛ ደረጃ ፍ/ቤት፤**

   የፓርቲሽን እና የማጠናቀቂያ ሥራዎችን ለመስራት በተገባው ውል መሰረት በወቅቱ ባለመጠናቀቁ ለዘገየባቸው ቀናት የጉዳት ካሳ ብር 18,886.38 ገቢ ሳይደረግ ተገኝቷል፡፡

   **የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት፤**

   ፍ/ቤቱ ለህንፃ ግንባታ በገባው ውል መሰረት ግንባታው በወቅቱ ባለመጠናቀቁ ለዘገየባቸው ቀናት መሰብሰብ የሚገባው የጉዳት ካሳ ብር 5,279,007.38 ገቢ ሳይደረግ ተገኝቷል፡፡

**ወጪ፤**

2. **በጠቅላይ ፍርድ ቤት፤** በድጋሚ ግልጽ ጨረታ ሳይወጣና በቂ ተወዳዳሪዎች ሳይቀርቡ በውስን ጨረታ የደንብ ልብስ ግዥ ለተፈፀመበት ብር 423,498.85 ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡
3. **ከፍተኛ ደረጃ ፍቤት፤**
   - ለፓርቴሽንና ለማጠናቀቂያ ስራ በሚል ከሶስት የስራ ተቋራጮች የዋጋ ማወዳደሪያ ሳይሰበሰብ በቀጥታ ለተፈፀመ የአገልግሎት ግዥ በድምሩ ብር 356,347.67 ወጪ መደረጉ ታውቋል፡፡
   - ለፓርቲሽን እና ለማጠናቀቂያ ስራ የውል ዋጋው 30 በመቶ ብር 106,904.29 ቅድሚያ ክፍያ መከፈል ሲገባው ብር 235,200.00 በመከፈሉ በብልጫ ብር 128,295.71 ወጪ መደረጉ ታውቋል፡፡

4. **የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት:** አቅራቢዎች ሳይወዳደሩ በቀጥታ ግዥ ከተለያዩ ድርጅቶች የፎቶ ኮፒ ማሽን የጥገና አገልግሎት ለተከናወነበት ብር 303,073.10 ተከፍሎ ተገኝቷል።

5. **አለአግባብ የትርፍ ሰዓት ክፍያ ብር 99,181.50 ተከፍሎ ተገኝቷል።**

**በጠቅላይ ፍ/ቤት:**

የበጀት ዓመቱን የንብረት ቆጠራ ለመስራት ኮሚቴዎችን በማቋቋም በመደበኛ የስራ ቀናት እንዲሁም ቅዳሜና እሁድን ጨምሮ 5 ሰራተኞች እያንዳንዳቸው ለ30 ቀናት ለሰሩበት በቀን ብር 50.00 በድምሩ ብር 7,500.00 ከመመሪያ ውጭ የትርፍ ሰዓት ተከፍሎ ተገኝቷል።

**በመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት፤**

ለንብረት ስራ አመራር አገልግሎት ክፍል ሰራተኞች እና የበጀት ዓመቱን እቅድ ለመስራት ኮሚቴዎችን በማቋቋም በመደበኛ የስራ ቀናት እና ቅዳሜ እና እሁድ ለሰሩበት በሚል በድምሩ ብር 91,681.50 ያለ አግባብ የትርፍ ሰዓት ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል።

6. **በከፍተኛ ፍ/ቤት፤** በ27 የወጪ ማስመስከሪያዎች በድምሩ ብር 273,435.55 የውሎ አበል ተከፍሎ መገኘቱንና የውሎ አበል መጠየቂያና መፍቀጃ ቅጽ ላይ መነሻ ቀን፤ መመለሻ ቀን፤ ሰዓት እና የቆዩበት ቀን ብዛት ሳይገለፅ ክፍያው በመፈፀሙ ወጪው ለመ/ቤቱ አገልግሎት መዋሉን ለማረጋገጥ አልተቻለም።

7. **በጠቅላይ ፍ/ቤት፤** ለፍ/ቤቱ የቀድሞ ፕሬዘዳንት እና ም/ፕሬዘዳንት ለውጭ አገር ህክምና የተከፈለ በድምሩ ብር 681,123.00 የወጪ ማስረጃው ሳይቀርብ ሂሳቡ በወጪ ተይዞ መገኘቱ በኦዲት ወቅት ታውቋል።

8. **በጠቅላይ ፍርድ ቤት፤** ለ2011 በጀት አመት ለዘጠኙ ክልሎች የተመደበው በጀት ብር 2,999,825.76 በፍርድ ቤቱ በተሰብሳቢ ተይዞ የተላከ ቢሆንም በክልሎች በተለያዩ የሂሳብ መደቦች ወጪ ተደርጎ ሂሳቡ ሲወራረድ በጠቅላይ ፍ/ቤት በጥቅል በሂሳብ መደብ 6412 (2631101) በወጪ ተመዝግቦ መገኘቱ ታውቋል፡፡

9. **በጀት ዓመቱን ያልጠበቀ ወጪ ብር 161,579.93 ተመዝግቦ ተገኝቷል።**

**ከፍተኛ ፍ/ቤት፤**

ከግንቦት/ 1/2010 እስከ ሰኔ 9/2010 ለቤንዚንና የናፍታ ግዥ ክፍያ ብር 73,290.10 እንዲሁም የመብራት አገልግሎት ክፍያ ብር 8,860.05 በድምሩ ብር 82,150.15 የበጀት ዓመቱን ሳይጠብቅ ከ2011 በጀት ዓመት ፍጆታ ጋር አብሮ መከፈሉን ለማወቅ ተችሏል።

**የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት፤**

ከጥቅምት/2007 እስከ ሰኔ/2010 ዓ.ም የተጠቀመበት የሶስት አመት ከዘጠኝ ወር የውሃ ፍጆታ ፍ/ቤቱ ከሐምሌ/2010 እስከ ህዳር 2011 ከተጠቀመበት የበጀት ዓመቱ የፍጆታ ሂሳብ ጋር እንዲከፈል በመደረጉ ብር 79,429.78 በጀት ዓመቱን ሳይጠብቅ ወጪ መደረጉ ታውቋል፡፡

10. **የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት፤** ፍ/ቤቱ ከከሳንታማሪያም ኮንስትራክሽን ኃ.የተ.የግ.ማህበር ጋር በገባው ውል መሰረት ከጠቅላላ ስራው አምስት በመቶ ብር 3,691,620.64 ላይ ሀምሳ በመቶ ብር 1,845,810.32 ለስራ ተቋራጩ እንዲለቀቅ እና ቀሪው ሀምሳ በመቶ ለግንባታ ስራው ጥራት ዋስትና ለአንድ ዓመት ተይዞ እንዲቆይ መደረግ ሲገባው ከመመሪያ ውጭ የመጨረሻ ክፍያ ሲፈጸም ለተቋራጩ ብር 1,845,810.32 ተከፍሎ ተገኝቷል ፡፡

11. **በጠቅላይ ፍርድ ቤት፤** ፍ/ቤቱ ከካፍ ማተሚያ ቤት ለሰበር ውሳኔ ቅጽ 13 የህትመት ግዥ ክፍያ ሲፈፀም የተጨማሪ እሴት ብር 89,284.43፤ ሳይቀነስ ሙሉ ክፍያ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡

ከላይ ከተራ ቁጥር 1 እስከ 11 በተገለጹት ጉልህና መሠረታዊ ልዩነቶች የተነሳ በእኛ አስተያየት የመ/ቤቱ የሂሳብ ሪፖርቶች ሰኔ 30 ቀን 2011 ዓ.ም. የተመለከተውን የፋይናንስ አቋም እና የበጀት ዓመቱን የሥራ እንቅስቃሴ በኢትዮጵያ መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ እንዲሁም የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት በአጥጋቢ ሁኔታ አያሳዩም፡፡

**ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች፤**

ቀጥሎ የተመለከቱት ጉዳዮች ትኩረት ሊደረግባቸው፤ እርምጃ ሊወሰድባቸው እና ለወደፊቱም ጥንቃቄ ሊደረግባቸው ይገባል፡፡

12. **የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት፤** ፍ/ቤቱ ከደመራ ኢንጂነሪንግ ጋር ለገባው የህንጻ ግንባታ ውል ለተከፈለው ብር 2,429,468.47 ቅድሚያ ክፍያ የቀረበው የባንክ ዋስትና መያገ ያልታደሰ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

13. **የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት፤**

ዓመታዊ የሲቪል ሰርቪስ ቀን በዓልን ለማክበር በሚል ያለአግባብ የምሳ ግብዣ ከነሙሉ መስተንግዶ ለተደረገበት የተከፈለ ብር 321,000.00 እንዲሁም በበጀት ዓመቱ መልካም ስራ ለሰሩ ሰራተኞች ለሽልማት በሚል ለ75 ሰዎች የገንዘብ ስጦታ ወጪ

የሆነ ብር 112,500.00 በድምሩ ብር 433,500.00 የወጪ ቅነሳ መመሪያን ያልተከተለ ክፍያ በመፈፀሙ አለአግባብ ወጪ መደረጉ ታውቋል፡፡

14. **<u>የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት</u>፤** የመደበኛ በጀት ብር 10,110,003.58፤ሥራ ላይ ያልዋለ ተገኝቷል፡፡

15. **<u>ከፍተኛ ፍ/ቤት</u>፤** በሂሳብ መደብ 6326 ከተፈቀደው የካፒታል በጀት ብር 56,083,976.19 ውስጥ ብር 50,000,000.00 ሥራ ላይ ያልዋለ ተገኝቷል፡፡

16. **<u>ጠቅላይ ፍ/ቤት</u>** በሂሳብ መደብ 6323 የተፈቀደው የካፒታል በጀት ብር 4,597,143.50 ያልተሰራበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

**<u>የሂሳብ ሪፖርት፤</u>**

17. የ2011 በጀት ዓመት የከፍተኛ እና የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤቶች የሂሳብ ሪፖርት በጠቅላይ ፍ/ቤት የበጀት መለያ ቁጥር (ኮድ)122 በጀት ተፈቅዶላቸው ሂሳባቸውን ለገ/ሚ/ር በማቅረባቸው እና ጠቅላይ ፍ/ቤት በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ባቀረበው የሂሳብ ሪፖርት ሂሳባቸው ያልተካተተ በመሆኑ የተጠቃለለ የሂሳብ ሪፖረት አለመቅረቡ ታውቋል፡፡ ለወደፊቱ በተሰጠው ግዜ ውስጥ የፍርድ ቤቶች የተጠቃለለ ሪፖርት መቅረብ ይኖርበታል፡፡

**<u>ሌሎች ጉዳዮች፤</u>**

**<u>ንብረት፤</u>**

**<u>በጠቅላይ ፍ/ቤት፤</u>**

በርካታ ኮምፒውተሮች የተለያዩ አይነት ወንበሮች፤ ምንጣፎች፤ ቢን ካርድ እና ስቶክ ካርዶች የሌሏቸው ወይም ያልተዘጋጀላቸው መሆኑን እና ከአገልግሎት ውጭ ሆነው ሊወገዱ የሚገባቸው እና አገልግሎት የሚሰጡ ዕቃዎች ሳይለዩ በአንድ ላይ ተከማችተው ተገኝተዋል፡፡

**<u>በከፍተኛ ፍ/ቤት፤</u>**

1. የተለያዩ አይነት የፎቶ ኮፒ እና የፕሪንተር ቀለሞች፤ 636 ደስጣ የፕሪንተር ወረቀቶች እና በርካታ ጎማዎች የቢንካርድም የስቶክ ካርዶችም የሌላቸው (ያልተከፈተላቸው) መሆኑ፤
2. አገልግሎት የማይሰጡ በርካታ ኮምፒውተሮች፤ ላፕቶፖች 12 የተበላሹ የፎቶኮፒ ማሽኖች፤ በርካታ ፕሪንተሮች፤ በርካታ UPS የድምጽ መቅረጫዎች የስልክ ቀፎዎች እና የመኪና መለዋወጫዎች የቢንካርድም የስቶክ ካርዶችም የሌላቸው

(ያልተከፈተላቸው) ሲሆን በተጨማሪም አገልግሎት የማይሰጡ ንብረቶች ተለይተው ያልተወገዱ መሆኑ በኦዲት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

**በመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት፤**

3. በርካታ ኮምፒዩተሮች፤ በርካታ የተለያዩ አይነት ቀለሞች፤ እስፒከሮች፤ የማይክ ማስቀመጫዎች፤ 4 የምንጣፍ ማጽጃ ማሽኖች፤ የተለያዩ የኤሌክትሮኒክስ እቃዎች በተጨማሪም በ2009 እና በ2010 በጅት ዓመት የተገኙ ዕቃቆች እርምጃ ሳይወሰድባቸወ በዕቃ ግምጃ ቤት ተከማችተው ተገኝተዋል፡፡

**በከፍተኛ ደረጃ ፍ/ቤት፤**

4. ለስራ ከሚያስፈልገው መጠን በላይ የተለያዩ ንብረቶች በቆጠራ እንዳይካተቱ በሰኔ/2011 መጨረሻ በተለያዩ ግለሰቦች ስም ፎቶኮፒ ወረቀት ፤የተለያዩ እስክሪፕቶዎች ሰማያዊ፤ ጥቁር፤ ቀይ፤ የተለያዩ ቶነሮች TK410; GPR 18: 505H፤ 05A; 55A; 49A; 6054 ; የተለያዩ መጠረዣዎች የመሳሰሉት የጽ/መሳሪያዎች ወጪ መደረጋቸውን፤

**ጠቅላይ ፍ/ቤት፤**

5. የሰሌዳ ቁጥር 4-05685 ለ3 ዓመት፣ 4-01007 ለ2 ዓመት፣ 4-01961 ለ2 ዓመት፣ 4-04207 ለ3 ዓመት፣ 4-07833 ለ3 ዓመት፤ 4-08031ለ3 ዓመት፣ 4-0701ለ3 ዓመት፣ 2-41866 ከ10 ዓመት በላይ፣ 4-24357 ከ10 ዓመት በላይ፣ እና 4-044138 ከ2 እስከ 4 ዓመት 4-04138 እንዲሁም 4-03827 ለ3 ዓመት ጋራዥ ቆመው የሚገኙ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡
6. በልደታ አካባቢ በሚገኝ ግቢ ውስጥ በሰሌዳ ቁጥር 1፤2፤ እና 3 የተመዘገቡ 51 ተሽከርካሪዎች 2 ባጃጆች ሁለት የውሃ መሣቢያ ማሽኖች በልደታ አካባቢ በአንድ ግቢ የሚገኙ መሆኑንና ለበለጠ የንብረት ጉዳት መጋለጣቸውን በኦዲት ለማወቅ ችለናል፡፡

**በከፍተኛ ደረጃ ፍ/ቤት፤**

7. በብልሽት ምክንያት ከአገልግሎት ውጪ ሆነው የቆሙ ተሽከርካሪዎች ኮድ 4-01093 ከ 3 ዓመት በላይ፤ ኮድ 4-03230 ፤4-8024፤4-14469፤ 4-3217 ከ 2 ዓመት በላይ እና በ2010 በጀት ዓመት ኦዲት እርምጃ እንዲወስድ አስተያየት ተሰጥቶባቸው የነበሩ ቢሆንም አሁንም ምንም አይነት እርምጃ ሳይወሰድ መገኘታቸውን፤
8. ኮድ 4-04166 ፤ 4-03146 አመት ያልሞላቸው እና ሞተር ሳይክል ኮድ 4-0207 ኮድ፣ 4-3639 እና ኮድ 4-12281 የካቲት 2011፤ 4-27264፤ 4-03061 በጥቅምት 2012፤ ኮድ 4-12282፤ ከ 15/ቀናት በፊት ረጅም ግዜ የቆሙ መሆናቸው፤

በመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት፤

9. በብልሽት ምክንያት ከአገልግሎት ውጪ የሆኑ ተሽከርካሪዎች በጋራዥ ውስጥ ለረዥም ግዜ መቆየታቸውን በኦዲት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

ከሠላምታ ጋር

ትዕግስት ሬታ
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች
ኦዲት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር